# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE ELEVEN: መወሰኛ ሰዓት

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ወ/ሮ ሉሊት TALKS TO ምህረት ABOUT HER NIGHTMARE**

- **ምህረት (F, 15)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**
- **አቶ ሙላቱ (M, 45)**

**SCENE 2: ዳንኤል MEETS ምህረት BEFORE CLASSES**

- **ዳንኤል (M, 15)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 3: ወ/ሮ ሉሊት GOES TO THE POLICE STATION**

- **ፖሊስ ሙሉጌታ(M, ?)**
- **ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)**

**SCENE 4: ንጉሴ REPORTS ዳንኤል TO ርዕሰ መምህርት ሰብለ**

- ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)
- ንጉሴ (M, 15)

1. INTRO- NARRATOR

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ሶስት አፍሪቃውያን አዳጊ ተማሪዎች ትክክለኛ የህይወት አቅጣጫን ለማግኘት ሲጥሩ የሚያሳያን ተከታታይ የራድዮ ድራማ ክፍል አስራ አንድ ነዉ። እስኪ ወደ ኋላ መለስ ብለን እስከዛሬ ምን እንደተከናወነ እንናስታዉስ፥

ዳንኤል እና ንጉሴ ምህረትን አፍቅረው ሁሉቱም የፍቅር ደብዳቤ ጽፈውላታል። ንጉሴ የላከላት ደብዳቤ በማራኪ የፍቅር ቃላት የተሞላ ሲሆን፤ ዳንኤል ደግሞ በፖስታ ዉስጥ ገንዘብ ጨምሮ ነዉ የላከላት። ይኸዉ ነገር ታድያ አስቸጋሪ ነገር ሳይፈጥር የቀረ አይመስልም!

2. ዳንኤል (EP 10, 35): “አይሆንም፣ ንጉሴ፣ ጓደኛማቾች መሆን አንችልም። (…) ይህ ስለ ምህረት ከሆነ ምህረት ስለራሷ እንድትወስን ተዋት።”

3. ንጉሴ: “አንተ ጂል! እዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ ህይወትህን አመሰቃቅዬው በመምጣትህ ትጸጸታለህ!”

እስከ አሁን ምህረት ለሁለቱም መልስ አልሰጠችም። ግን ከእናቷ ጋር ልብ ለልብ በግልጽ በመነጋገርዋ ለአንደኛው ልቧ ፈቅዷል።

4. ምህረት (EP 09, 109): “ባየኝ ቁጥር… ሳየው…ሆዴ ይታወክብኛል።”

የምህረት እናት፣ ወ/ሮ ሉሊት ፣ ለጊዜው ችግር ላይ ናቸው። ከአክስትየው፣ ከወ/ሮ ለምለም ፣ ማለት ከባለቤታቸው እህት ጋር ላቦሪያ ውስጥ ይኖራሉ የተባሉት ሁለቱ የአብራካቸው ክፋይ የሆኑት ልጆቻቸው ናፍቀዋቸዋል። እውነታው ግን ወ/ሮ ለምለም መንትያዎቹን ልጆች ከመንከባከብ ይልቅ፣ በወርቅ ማዕድን ማውጫ ውስጥ እንዲሰሩ ልካቸዋለች። ሁለቱ ልጆች ከጥቂት ቀናት በፊት በመጥፋታቸዉ የት እንደደረሱ አልታወቀም። ወ/ሮ ለምለምም ልጆቹ እንደጠፉ ለወንድሟ አቶ ሙላቱ በአጭር መልዕክት አሳውቃዋለች። ታዲያ ይህን ዜና አቶ ሙላቱ ለምህረት እና ለወ/ሮ ሉሊት እንዴት ሊያረዷቸው ይችላሉ? እስኪ "መወሰኛ ሰዓት" የተሰኘዉን የድራማውን አስራ አንደኛ ክፍልእንከታተል። ግዜዉ ምሽት ነዉ፤ አቶ ሙላቱ እስከ አሁንም ከቡና ቤት አልተመለሱም። ወ/ሮ ሉሊት ስለ ሁለቱ ወንዶች ልጆቻቸው አቃዠቷቸዋል። እናም ድንገት ነቅተው በፍጥነትb ወደ ምህረት ክፍል ይሄዳሉ።

**<u>SCENE 1: ወ/ሮ ሉሊት TALKS TO ምህረት ABOUT HER NIGHTMARE</u>**

5. **NIGHT ATMO**
6. **SFX: <u>ወ/ሮ ሉሊት</u> ENTERS - FAST FOOTSTEPS**
7. **SFX: LIGHT BEING SWITCHED ON (HUMMING SOUND OF THE LIGHT)**

8. **<u>ምህረት:</u>** **(sleepy voice)** እማዬ፣ ምንድን ነው? እንቅልፍ ሸለብ እያደረገኝ ነበር።ምን ነዉ መብራቱን አበራሽው?

9. **<u>ወ/ሮ ሉሊት</u> :** **(breathing heavily)** መተኛት አልቻልኩም፣ ምህረት፤ አስፈሪ ቅዠት ነበር።

10. ምህረት: ምን ነው እማ? እስኪ ተቀመጭ ። ታድያ እኮ አሁንም አልተሻለሽም።

11. ወ/ሮ ሉሊት : አስፈሪ ህልም ነው ያየሁት። ወንድሞችሽ ላይ የሆነ ክፉ ነገር ሲደርስባቸው አለምኩ! ምን እንደሆነ አላውቅም፣ ብቻ የሆነ ክፉ ነገር እንዳለ ይሰማኛል።

12. ምህረት: (comforting) እማዬ፣ ህልም ብቻ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። እንዲህ ከተጨነቅሽ ታዲያ ለምን አክስቴ ወ/ሮ ለምለም ጋር ደውለሽ ቅዱስ እና ብሩክ እንዴት እንደሆኑ አትጠይቂያትም?

13. ወ/ሮ ሉሊት : ልክ እንደነቃሁ ብደዉልላትም ስልኳን አታነሳም።

14. ምህረት: እማዬ፣ አለማንሳትዋ አይገርመኝም። መሽቷል እርሷም ሆነ ወንድሞቼ በግዜ ተኝተው ሊሆን ይችላል። ጠዋት እንደገና ሞክሪ።

15. SFX: KNOCKING ON FRONT DOOR

16. አቶ ሙላቱ : (standing outside, drunk voice) ወ/ሮ ሉሊት ክፈቺ! አንዴ ክፈቺ። አሊባባ ነኝ! (shouts loudly) ክፈቺ!

17. ወ/ሮ ሉሊት : እስከ ነገ መቆየት አልችልም። እስከ ነገ ቢቆይ ሊዘገይ ይችላል።

18. ምህረት: እማ፣ አሁን እኔንም እያስጨነቅሽኝ ነው። ግን እስኪ እስኪ ነጋ እንቆይ ! እኔ በበኩሌ ወንድሞቼ ምንም እንዳልሆኑ እርግጠኛ ነኝ።.

19. SFX: MORE KNOCKING ON DOOR

20. አቶ ሙላቱ : በሩን ክፈቺ ብያለሁ! ምን እየጠበቅሽ ነው? ዘራፊዎች መጥተው ማንቁርቴን እንዲይዙ ነው?

21. ምህረት: እማዬ፣ብትከፍቺለት እና ቢገባ ይሻላል። አለበለዚያ ሌሊቱን ሰላም አናገኝም። ፡

22. ወ/ሮ ሉሊት : መልካም ሌሊት፣ ምህረቴ።.

23. SFX: LIGHT SWITCHED OFF

24. ወ/ሮ ሉሊት : ቆይ አንዴ፣ ሙላቱ, እየመጣሁ ነኝ።

25. አቶ ሙላቱ : እየመጣሽ? እየመጣሽ ነዉ? የገዛ ደጃፍሽ ጋር ለመድረስ አውቶቡስ መያዝ አስፈለገሽ?

26. SFX: DOOR BEING UNLOCKED

27. አቶ ሙላቱ : በስተመጨረሻ መልስ አገኘን,,,,እስቲ የሚበላ ነገር ስጪኝ።

28. SFX: DOOR BEING LOCKED

29. ወ/ሮ ሉሊት : ሙላቱ፣ ዛሬ ሌሊት አስፈሪ ህልም ነው ያየሁት ሲያቃዠኝ ነበር እና ...

30. አቶ ሙላቱ : (not interested) የሚበላ ነገር አለሽ??

31. ወ/ሮ ሉሊት : (desperate) ሙላቱ፣ ስማኝ እኮ ነዉ የምልህ! አስጨናቂ ህልም ነው ያየሁት፤ ልክ እኮ...--

32. አቶ ሙላቱ : (cuts her short) ሉሊት ደደብ አትሁኚ! ሂጂ እና ምግብ አምጪልኝ። ከእህቴ ለምለም ሰምቻለሁ። ታውቂያለሽ፤ አትወድሽም። መጥፎ ቀልድ እየቀለደችብሽ ነው......

33. ወ/ሮ ሉሊት : (curious) ከለምለም ሰምተሀል? አምላኬ! ምን አለችህ! ስለ ቅዱስ እና ብሩክ የተናገረችው ነገር አለ?

34. SFX: አቶ ሙላቱ SITTING ON SOFA

35. አቶ ሙላቱ : (drunk) አዎ። ግን የምር እንዳይመስልሽ። አንዳንዴ እሷ ትጃጃላለች።.

36. ወ/ሮ ሉሊት : (still very curious) ባክህን፣ ሙላቱ ምን እንዳለች ንገረኝ። ብቻ ንገረኝ……

37. አቶ ሙላቱ : ልጆቹ ጠፍተዋል ብላ ጻፈችልኝ።.

38. ምህረት: ምን?

39. ወ/ሮ ሉሊት : (utterly shocked) ዉይ አምላኬ! ምህረት! ህልሜ እውነት ነው!

40. ምህረት: ምንአልባት አባቴ ትክክል ሊሆን ይችላል። አክስቴ ለምለም እየቀለደች ነበር።

41. ወ/ሮ ሉሊት : የሆነ ነገር ማድረግ አለብኝ!

42. አቶ ሙላቱ : አሁን የሚበላ ነገር አምጪልኝ! እና ደግሞ ምህረት-ሂጂ አሁኑኑ ተኚ! ጎረቤቱን ሁለታችሁ እየበጠበጣችሁ ነው!

43. MUSIC INTERLUDE

## SCENE 2: ዳንኤል MEETS ምህረት BEFORE CLASSES

**44. SFX: SCHOOL ATMO IN CORRIDOR**

**45. ዳንኤል:** ምህረት፣ ስለተገናኘን ደስ ብሎኛል፡፡ ክፍል ውስጥ ስላልነበርሽ ናፍቀሽኝ ነበር፡፡ ምን ሆነሽ ነዉ? አሁን ተሻለሽ?

**46. ምህረት:** ደህና ነኝ፣ ዳንኤል፣ ስለጠየከኝ አመሰግናለሁ፡፡ ወደ ትምህርት ቤት መመለሴም ጥሩ ነዉ፡፡

**47. ዳንኤል:** እና ስለላኩልሽ ስጦታ ምን አሰብሽ? ወደድሽው? ምንም ያልሽኝ ነገር የለም፡፡

**48. ምህረት:** ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም፣ ዳንኤል ...ከዚህ ቀደም ማንም ሰው ይህን ያህል ገንዘብ ሰጥቶኝ አያውቅም፡፡

**49. ዳንኤል:** ማለቴ፣ ምን አልባት ገንዘብ ያስፈልጋታል ብዬ አስቤ ነው፡፡ በሌላ አታስቢ-በገንዘብ ልገዛሽ ወይም ላባብልሽ ፈልጌ አይደለም።

**50. ምህረት:** ምንም አይደለም፣ ዳንኤል፡፡ ግን እባክህን፣ እንዳይለምድብህ፡፡ የአሁኑን አመሰግናለሁ-ተቀብዬዋለሁ፣ ግን ይሄ ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ ነው፡፡

**51. ዳንኤል:** (chuckles) እሺ፣ ቃል እገባልሻለሁ፡፡ በጥሬ ገንዘብ ስጦታ አላቀርብም ብዬ ቃል እገባለሁ፡፡ ግን ሌላ የሆነ ነገር ልገዛልሽ እችላለሁ፣ አልችልም? ልክ ...ታውቂያለሽ...ሴቶች ልጆች ስጦታ ይወድዳሉ፡፡

52. ምህረት: ስትናገር ብዙ ልምድ እንዳለው ሰው ነው። ለመሆኑ ከዚህ በፊት ስንት የሴት ጓደኞች ነበሩህ?

53. ዳንኤል: (caught off guard) እኔ? የሴት ጓደኞች? ኧረ ...እውነት ለመናገር ምህረት፣ አንቺ በእውነት ...እም...የመጀመሪያዋ የተማረኩብሽ አንች ነሽ።

54. ምህረት: (shyly) በእውነት? እንዴት አምንህለሁ? የመጣኸው ከሌላ ቦታ ነው። ምንአልባት ላቦሪያ ውስጥ የምትጠብቅህ ሴት ልትኖር ትችላለች።

55. ዳንኤል: እውነት ነው የመጣሁት ከሌላ ቦታ ነው። እና ላቦሪያ ውስጥ ብዙ ቆንጆ ሴቶች አሉ። ግን አንዳቸውም ከአንቺ ጋር መወዳደር አይችሉም። ማለቴ ሁሉም ነገርሽ እንከን አይወጣለትም።

56. ምህረት: (Giggles) አመሰግናለሁ፣ ዳንኤል።

57. ዳንኤል: ምህረት፣ ግን የሆነ ነገር ማወቅ እፈልጋለሁ። እንደኔ ይሰማሻል? እባክሽ እውነቱን ንገሪኝ። ስለ እኔ የሆነ ነገር ተሰምቶሽ ያውቃል?

KW BEGIN

58. ምህረት: ህምምም...ዳንኤል፣ አላውቅም። እርስ በእርስ እኮ ምንም ያህል አንተዋወቅም! እኔ የሆነ ጊዜ ያስፈልገኛል። በአሁኑ ወቅት በህይወቴ እየተከሰቱ ያሉ ብዙ ነገሮች አሉ...በተለይ እቤት ውስጥ ግን አሁን ስለዚህ ጉዳይ መናገር አልችልም።

59. <u>ዳንኤል:</u> ይገባኛል። ላስጨንቅሽ አልፈልግም። ግን አባክሽን፣ አባክሽን ልቤን አታሳዝኚው። እኔ...

60. <u>ምህረት:</u> ዳንኤል እንዲህ አትበል። የማንንም ልብ ማሳዘን አልፈልግም። ያንተንም ሆነ፣ የንጉሴን፣ የማንንም።

61. <u>ዳንኤል:</u> ግን ፈጥነሽ መወሰን ይኖርብሻል። አይተሽዋል አይደል? እንዲህ ሆነን መቼም ለዘላለም መዝለቅ አንችልም።

**KW END**

62. <u>ምህረት:</u> ዳንኤል-ለጊዜው በእውነት ግራ ገብቶኛል። ጊዜ እፈልጋለሁ፤ እባክህ ፤

**63. SFX: SCHOOL BELL RINGS**

64. <u>ዳንኤል:</u> ቢያንስ ከትምህርት ቤት በኋላ ወደ አውቶቡስ ማቆሚያው ልሸኝሽ እችላለሁ?

65. <u>ምህረት:</u> (confused) ኸ ...የምንችል ይመስለኛል ግን ትዕግስትም አብራን ልትኖር ትችላለች። ብዙውን ጊዜ ወደ ቤት የምንሄደው አብረን ነው። ቅር ካላለህ አብረኸን ልትሆን ትችላለህ።

66. <u>ዳንኤል:</u> በእውነቱ ትዕግስት አብራን መሆኗን አልወደድኩትም፣ ግን ላንቺ ስል አብሪያችሁ ብሄድ ደስ ይለኛል።

**67. MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 3: ወ/ሮ ሉሊት GOES TO THE POLICE STATION**

68. **SFX: POLICE STATION, SIREN FROM A DISTANCE**

69. ፖሊስ:ሙሉጌታ ቀጥይ! (short pause) እዛ ጋር ምን አንርዳሽ?

70. ወ/ሮ ሉሊት : እባክዎን፣ ሁለት ወንድ ልጆቼ መጥፋታቸውን ለማስመዝገብ ነው የመጣሁት።

71. **SFX: PEN WRITING ON PAPER**

72. ፖሊስ: እሺ፤ ሁለት ወንዶች ልጆች ጠፍተዋል። ስማቸው ማን ይባላል?

73. ወ/ሮ ሉሊት : ቅዱስ እና ብሩክ።

74. **SFX: PEN WRITING ON PAPER**

75. ወ/ሮ ሉሊት : ቅዱስ እና ብሩክ ሙላቱ፤መንታዎች ናቸው።

76. ፖሊስ: እሺ። እድሜያቸ ስንት ነው?

77. ወ/ሮ ሉሊት : ስምንት ዓመታቸው ነው።

78. **SFX : PEN WRITING ON PAPER**

79. ፖሊስ: ለመጨረሻ ጊዜ ያየሻቸው መቼ ነው? የለበሱትስ ምን ነበር?

80. ወ/ሮ ሉሊት : (nervous) የለበሱትን አላስታውስም። ለመጨረሻ ያየኋቸው ግን ከሶስት ወራት በፊት ነው።

81. ፖሊስ: (completely shocked) ከሶስት ወራት በፊት! እና መጥፋታቸውን የምታመለክቺው ዛሬ ነው?

82. ወ/ሮ ሉሊት : ይኖሩ የነበረዉ ላቦሪያ ውስጥ ከአክስታቸው ጋር ስለነበር ነዉ! መጥፋታቸውን ያወቅኩት ገና ትናንት ነው፡፤

83. ፖሊስ: አልገባኝም፡፡ እነዚህ ሁለት ልጆች ኪሲምባ ውስጥ አይደሉም እያልሽኝ ነው? ያሉት ላቦሪያ ነው ማለት ነው?

84. ወ/ሮ ሉሊት : አዎ፡፡ አክስታቸው ወስዳቸዋለች፡፡ ስሟ ወ/ሮ ለምለም ይባላል፡፡ ይህ የሆነዉ በባለቤቴ ሀሳብ ነበር፡፡ እኔ እንዲህ እንዲሆን አልፈለኩም ነበር…

85. ፖሊስ: በጣም አዝናለሁ፡፡ ብዙ ልንረዳሽ የምንችለው ነገር የለም፡፡

**KW BEGIN**

86. ወ/ሮ ሉሊት : (bit scared) ተስፋ ያደረኩት ምንአልባት እዛ ላሉ ፖሊሶች ነግራችሁ እነርሱ ይፈልጓቸዋል ብዬ ነበር፡፡

87. ፖሊስ: አዝናለሁ፡፡ ልንረዳሽ አንችልም፡፡ እባክሽን የእኔ እመቤት ጨርሰናል፡፡ (calls out) ተረኛ!

88. **SFX: PAPER BEING RIPPED OFF PAGE AND THEN CRUMPLED AND THROWN AWAY**

**89.** <u>ወ/ሮ ሉሊት :</u> **(starts to cry)** አይሆንም፣ አባክዎ፣ አይሆንም፣ አባክዎ መረጃውን አይወርውሩት። አባክዎ፣ ልጆቼ ይፈልጉኛል! እራሴ ብቻዬን እንዴት እንደምፈልጋቸው አላውቅም። ጌታዬ፣ አባክዎ!

**90.** <u>ፖሊስ:</u> **(calls out)** ተረኛ!

**KW END**

**91.** <u>ወ/ሮ ሉሊት :</u> አባክዎ ጌታዬ፣ ሊረዱኝ ይገባል። እስካልረዱኝ ድረስ ከእዚህንቅንቅ አልልም።

**92.** <u>ፖሊስ:</u> አሁን እንደዚህ አይነት ጨዋታ ለመጫወት ፍለላጎቱ የለኝም! አስር አለቃ ይህቺን ሴት ወስደህ እስር ቤተ ወርውርልኝ። ስትረጋጋ እንድትሄድ ትለቅቃታለህ።

**93.** <u>ወ/ሮ ሉሊት :</u> **(desperate crying)** ኧረ አይሆንም! አባክዎን!

**94. SFX STEPS CORPORAL**

**95. SFX HAND CUFFS**

**96. MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 4: ንጉሴ REPORTS ዳንኤል TO PRINCIPAL ርዕሰ መምህርት ሰብለ**

**97. SFX: KNOCKING ON DOOR**

**98.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : ይግቡ፣

**99.** ንጉሴ: እንደምን ዋሉ፣ መምህርት

**100.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : እንደምን ዋልክ ንጉሴ፣ ምን ተፈጠረ? ምን ልርዳህ?

**101.** ንጉሴ: አያይ... ስለ አንድ ሰው ለመናገር ነው የመጣሁት.

**102.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : እሺ ፤ ቀጥል፤ እየሰማሁህ ነው።

**103.** ንጉሴ: ይሄ.. ዳንኤል የሚባል ልጅ አያከብረኝም። ግትር፣ የማይታዘዝ በዛ ላይ በጥባጭ ተማሪ ነው።

**104.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : እሺ፤ እና ሌሎቹ ልጆች ስለእሱ ምን ያስባሉ? ይወዱታል? የተለዩ ጓደኞች ወይም አንድ ጓደኛ አለው?

**105.** ንጉሴ: ችግሩ ያ ነው። መምህርት ብዙዎቹ ተማሪዎች አይወዱትም። ያዉቁ እንደሆነ፣ የመጣው ከላቦሪያ ነው፤ የተለየ ለመመምሰል፣ የተለየ ለመናገር፣ የተለየ ለማሰብ ይሞክራል። ከሌሎቻችን ጋር አይገጥምም።

**106.** ርዕሰ መምህርት ሰብለ : ንጉሴ፤ አንተ በእኔ ቦታ ብትሆን፣ ፣ ምን ታደርግ ነበር?

**107.** ንጉሴ: (maliciously) ወደ እዛ ወደመጣበት ወደ ላቦሪያ እመልሰው ነበር።

**108. MUSIC INTERLUDE**

**109. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>**

የንጉሴ የበቀል ድርጊት “መንታ መንገዶች ላይ ያለ ትውልድ” የተሰኘው ድራማ አስራ አንደኛ ክፍል መጨረሻ ላይ አድርሶናል፡፡ ርዕሰ መምህርት ሰብለ ንጉሴን አምነዉ ዳንኤልን ይቀጡት ይሆን? ወ/ሮ ሉሊትስ ያለ ፖሊስ ትብብር እንዴት ልጆቻቸውን ያገኙ ይሆን? ዳንኤልስ? ስሜቱን ለምህረት ተናዝዟል፣ ግን የእውነቱን ይሆን? የተወሰነም ፍንጭ ቢሆን ዳንኤል ከቀረፀው የቪዲዮ ዘገባው ድረ-ገጻችን ውስጥ ታገኙ ይሆናል፤ ዘገባውን ተከታተሉ። የዛሬዉን ድራማ በድጋሚ ማድመጥ ከፈለጉ በድረ-ገጽ አድራሻችን dw.de/lbe ላይ ያገኙታል። ድራማዉን በግል መዝገቦ ላይም ለመገልበጥ ይችላሉ። በፌስ ቡክ ገጻችን ላይም ሊከታተሉን እንደሚችሉ አይዘንጉ። በድጋሚ እስክንገናኝ ድረስ ጤና ይስጥልን!.